የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ–ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9[th] Year No. 26
ADDIS ABABA–17[th] January, 2003

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የኢትዮጵያ አየር መንገድ ድርጅት ማቋቋሚያ (ማሻሻያ)
ደንብ ........................................................ ገጽ ፪ሺ፷፯

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 81/2003
Ethiopian Airlines Enterprise Establishment
(Amendment) Regulations .................. Page 2067

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፩/፲፱፻፺፭
## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ድርጅት
## ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፬) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ አየር መንገድ ድርጅት ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፹፩/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲፮/፲፱፻፹፯ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

አንቀጽ ፯ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፯ ተተክቷል፤

"፯· ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፪ ቢሊዮን ፭፻ ሚሊዮን (ሁለት ቢሊዮን አምስት መቶ ሚሊዮን) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፩ ቢሊዮን ፬፻፩ ሚሊዮን ፩፻፳፩ሺህ ፰፻፳፭ ብር (አንድ ቢሊዮን አራት መቶ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሃያ አምስት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል"።

፫· ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

Council of Ministers Regulations No. 81/2003

## ETHIOPIAN AIRLINES ENTERPRISE ESTABLISHMENT (AMENDMENT) REGULATIONS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Power and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia proclamation No. 4/1995 and Article 47 (4) of the Public Enterprises Establishment Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

   These Regulations may be cited as the "Ethiopian Airlines Enterprise Establishment (Amendment) Regulations No. 81/2003".

2. *Amendment*

   The Ethiopian Airlines Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 216/1995 are amended as follows:

   "7. *Capital*

   The authorized capital of the Enterprise is Birr 2,500,000,000 (Two Billion, five Hundred Million) of which Birr 1,401,121,825 (One Billion, Four Hundred One Million, One Hundred Twenty One Thousand Eight Hundred Twenty Five) is paid up in cash and in kind".

3. *Effective Date*

   These Regulations shall come into force as of the date of their publication in the Federal Gazetta.

Done at Addis Ababa, this 17[th] day of January, 2003.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001